የCOVID-19 ክትባት ለሕፃናት እና ለትናንሽ ልጆች

ለወላጆች እና ለአሳዳጊዎች የተዘጋጀ ጥያቄዎች እና መልሶች






May 15, 2023

Public Health
Seattle & King County

የCOVID-19 ክትባት ልጅዎን በበሽታው ምክንያት ሆስፒታል እንዳይተኛ እንዲሁም ከረጅም ጊዜ የኮቪድ ምልክቶች ለመጠበቅ የሚከላከለው ምርጡ መንገድ ነው።

- በህፃናት እና በልጆች ላይ ያሉ አብዛኛዎቹ የ COVID-19 ክስተቶች ከባድ አይደሉም። ነገር ግን፣ አልፎ አልፎ፣ COVID-19 በሽታ በከባድ ህመመ ምክንያት ሆስፒታል ውስጥ እንዲተኙ የሚያደርጉ ወይም ወደ “ረጅም ኮቪድ ህመም” ሊያጋልጡ የሚችሉ ከባድ ኢንፌክሽኖችን ሊያስከትል ይችላል።

- ልክ እንደ መኪና ውስጥ እንደሚደረገው የልጆች መቀመጫ ማለት ነው፥ በሽታው ሊይዛቸው ቢችልም እንኳን ክትባቱ ሕጻናት ልጆችን ከከባድ አደገኛ ክስተቶች ይጠብቃቸዋል።



Public Health
Seattle & King County


ክትባቱ ልጆችን ልጆች እንዲሆኑ ይረዳል።

ልጆች የወቅታዊ ክትባቶቻቸውን ሲውስዱ፣ የሚወዷቸውን ብዙ ተግባራት፣ ለምሳሌ ቅድመ ትምህርት ቤት መሔድ እና ከጓደኞቻቸው እንዲሁም ከቤተሰባቸው ጋር እቤት ውስጥ አብረው ጊዜ ማሳለፍ ይችላሉ።



Public Health
Seattle & King County

የCOVID-19 ክትባት ልጆች ደህንነታቸውን ጠብቀው ከሌሎች ሰዎች ጋር አብረው እንዲሆኑ ይረዳል



ልጅዎን ማስከተብ፣ **የቤተሰብዎን አባላት እና የጓደኞችን ጤንነት ይጠብቃል፣** በተለይም ለከፍተኛ በሽታ ተጋላጭ የሆኑትን አባላት ለበሽታው እንዳይጋለጡ ይረዳል።

Public Health
Seattle & King County

የልጆች ክትባት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ ነው?



አዎ። ኤፍዲኤ (FDA) ክትባቱ በክሊኒካዊ ጥናቶች ውስጥ ምንም አይነት ከባድ የደህንነት ስጋት እንደሌለው ተረድቷል።

ከክትባቱ በኋላ ልጆች በCOVID በሽታ ሊያዙ ይችላሉ፣ ነገር ግን ክትባቱ የበሽታውን ህመም ቀላል እንዲሆን ይረዳል።

ክትባቱ በጣም አስፈላጊ ለሆኑት ነገሮች ለምሳሌ፣ ከሆስፒታል ከመተኛት፣ ከከባድ የጤና ችግሮች እና በበሽታው ምክንያት ከመሞት **ይከላከላል።**

Public Health
Seattle & King County

ሕፃናት እና ትናንሽ ልጆች ምን ዓይነት የCOVID-19 ክትባት ሊያገኙ ይችላሉ?



ዕድሜያቸው ከ6 ወር በላይ የሆኑ ህጻናት ልጆች የፋይዘርን (Pfizer) ወይም ሞደርናን (Moderna) COVID-19 ክትባት ሊወስዱ ይችላሉ።

Public Health
Seattle & King County

ሕጻኑ ወይም ትንሹ ልጄ ምን ያህል የክትባት ዙር መውሰድ አለበት?

እድሜያቸው ከ6 ወር እስከ 5ዓመት የሆኑ ህጻናት ብዙ COVID-19 ክትባት ሊፈልጉ ይችላሉ፣ ቢያንስ 1 የተሻሻለ የፒፋይዘር ወይም ሞደርና ክትባት። ቀደም ሲል በተቀበሉት የክትባት መጠን እና በእድሜ ላይ የተመሰረተ ነው።

ምን ያህል መጠን እንደሚፈልጉ ጥያቄዎች ካለዎት እባክዎን የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።



Public Health
Seattle & King County

ለህፃናት እና ለትናንሽ ልጆች የሚሰጡት ክትባት ውስጥ ምን አይነት ንጥረ ነገሮች/ ግብአቶች አሉት?

ገባሪ ንጥረ ነገሮች: mRNA (የእርስዎ ሴሎች ኮሮናቫይረስን በፍጥነት አውቀውት ጥቃት እንዲያደርጉበት የሚረዳ ሞለኪውል)

በ ፋይዘር (Pfizer) ውስጥ ያሉ ሌሎች ንጥረ ነገሮች፡ አሚኖ አልኮሆል፣ ቅባቶች (ቅባት)፣ሶዲየም ክሎራይድ (ጨው) እና ሱክሮስ (ስኳር)።

በሞደርና (Moderna) ውስጥ ያሉ ሌሎች ንጥረ ነገሮች፡ ሊፒድስ (ስብ) ፣ ሶዲየም አሲቴት እና ሶዲየም አሲቴት ትራይሃይድሬት (ጨው)፣ የአሲድ ማረጋጊያዎች እና ሱክሮስ (ስኳር)።

Public Health
Seattle & King County

ክትባቱ ለልጆች ነፃ ነው?

አዎ፣ የ**COVID-19 ክትባት ሁል ጊዜም ነፃ ነው።**

የኢንሹራንስ እና የኢሚግሬሽን ሁኔታ ምንም ይሁን ምን በ WA ውስጥ የሚኖሩ ልጆች የ COVID-19 ክትባቶችን **ያለ ምንም ወጪ** ይገኛሉ።



Public Health
Seattle & King County

ለሕጻናት እና ለትናንሽ ልጆች ምን አይነት የተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች አሉ?

አብዛኛውን ጊዜ የጎንዮሽ ጉዳቶች አንድ ወይም ሁለት ቀን ያህል ይቆያሉ። የተለመዱ የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤

- ክትባቱን የተወጉበት ቦታ ላይ ህመም
- መነጫነጭ እና ማልቀስ
- እንቅልፋም መሆን እና ድካም
- የምግብ ፍላጎት ማጣት



ብዙም ያልተለመደ የጎንዮሽ ጉዳቶች፡ ማቅለሽለሽ/ማስታወክ፣ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ የእጢዎች እብጠት።

እነዚህ ልጅዎት ሰውነታቸው ጥበቃን እየገነባ መሆኑን የሚያሳዩ **የተለመዱ ምልክቶች ናቸው።**

Public Health
Seattle & King County

በማዮካርዳይተስ (myocarditis) እና በልጆች ክትባት መካከል ግንኙነት አለ?



- በጉርምስና ዕድሜ ላይ በሚገኙ ወንዶች ላይ፣ የmRNA ክትባቶች ማዮካርዲስ (Myocarditis) ተብሎ ከሚጠራው **ያልተለመደ የልብ ጡንቻ መቆጣት** (ኢንፍልሜሽን) ክስተቶች ጋር ግንኙነት እንዳላቸው ታይቷል።
- ይህ ክስተት የCOVID ክትባታን ከወሰዱት ከ11 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ላይ **አልታየም**።

Public Health
Seattle & King County

በማዮካርዳይተስ (myocarditis) እና በልጆች ክትባት መካከል ግንኙነት አለ?

- ከ5 አመት በታች የሆኑ ህጻናት የሞደርናን (Modadia) ወይም የፋይዘርን (Pfizer) ክትባት **ሲወሰዱ** በተደረገው ጥናት ላይ ይህ ከስተት ምንም አይነት ሪፖርት አልተደረገም።
- ዕድሜያቸው ከ5 እስከ 11 አመት በሆኑ ልጆች ላይ የተደረገው ትልቅ የሀገር አቀፍ ጥናት ላይ እንደሚያሳየው ከሆነ ከክትባቱ ይልቅ **በCOVID-19 ምክንያት ማዮካርዲስ (myocarditis)** የመያዙ እድላቸው ከፍተኛ እንደሆነ ታይቷል።



Public Health
Seattle & King County

ለሕፃናት እና ለትናንሽ ልጆች የሚሆን ክትባት የት ማግኘት እችላለሁ?



ቀጠሮዎች በ ላይ ማግኘት ይችላሉ:

- የልጅዎት ሐኪም ቢሮዎች
- ክሊኒኮች
- የክትባት ቦታዎች

በተጨማሪም አንዳንድ ፋርማሲዎች ለትንንሽ ልጆች ክትባት መስጠት ይችላሉ።

በአቅራቢያዎ የሚገኝ የክትባት ቦታን ለማግኘት ወይም ቀጠሮ ለመያዝ

- ወደ **kingcounty.gov/vaccine/Amharic** ድህረገጽ ይሂዱ።
- የዋሽንግተን ግዛት COVID-19 የመረጃ መስመር በ **1-800-525-0127** ይደውሉ እና **#ን ይጫኑ።** (መስመሩን ሲያገኙ የመረጡትን ቋንቋ ይጠይቁ)

Public Health
Seattle & King County

ለልጄ የክትባት ቀጠሮ ለመዘጋጀት ምን ማድረግ አለብኝ?

ልጆትን አጭር እጅጌ ያለው ወይም ሰፋ ያለ ለመጠቅለል የሚመች **ልብስ** ያልብሱ።

ለልጆት እውነቱን ይንገሩ፡ መርፌው ለአንድ አፍታ ያህል ያማል ወይም እንደ መቆንጠጥ ያለ ስሜት አለው።

የልጅዎ ቀጠሮ ቀን እና ከክትባት በኋላ ለአጭር ጊዜ ለመጠበቅ የሚጠቀምበት **መጽሐፍ ወይም ትንሽ አሻንጉሊት ይዘው ይምጡ።**



Public Health
Seattle & King County

ለእኔ ወደ ክትባት ቦታው ለመሄድ ከባድ ነው። ምን እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?

ተደራሽነት: ለአካል ጉዳተኞች አቅርቦት፣ ኢሜል በ**publichealthaccommodations@kingcounty.gov** ላይ ያድርጉ

የቋንቋ እርዳታ: የዋሽንግተን ግዛት COVID-19 የመረጃ መስመር በ **1-800-525-0127** ይደውሉ እና **#ን ይጫኑ።** (መስመሩን ሲያገኙ የመረጡትን ቋንቋ ይጠይቁ)

መጓጓዣዎች: ለእርስዎ ወይም ለልጅዎ የክትባት ቀጠሮ መጓጓዣ ከፈለጉ፡ በ 425-943-6706 ይደውሉ (ከሰኞ እስከ አርብ፣ 8:30 am - 4 pm. ወይም www.FindARide.org ይጎብኙ።

Public Health
Seattle & King County



kingcounty.gov/vaccine/amharic

Public Health
Seattle & King County